በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# ታቱ - አካልን መነቀስና በተለያዩ ቀለማት መበጣት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዚያ ፳፫ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# ታቱ - አካልን መነቀስና በተለያዩ ቀለማት መበጣት

*መግቢያ*

- አንዳንድ ጊዜ እጃቸውን፤ አካላቸውን፤ ጀርባቸውን በተለያዩ ቀላማት በተሳሉ አውሬዎች… የሽፈኑ ወንዶች ይገጥሙናል፤ ያን ጨርሰን ዘወር ስንል አፍንጫዋ፡ ዓይንዋ፡ ጆሮዋ… ተበሳስቶ ብረታ ብረቶች የተንጠለጠሉባት ለማየትም የምታስጨንቅ ሴት ቆማም ይሁን ስታልፍ እናያለን፡፡ ከተቻለ ለወደፊቱ ይኽን የመሰለውን ነገር የተመለከትንበትን አካባቢ ተመልሰን ባንሄድበት እንመርጠዋለን - ነፍስን ያስጨንቃልና፡፡ #ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በዓመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና በዓመፀኞች ሴሰኛ ኑሮ የተገፋውን ያን ጻድቅ ካዳነ…; *2ኛ ጴጥ 2፡7-9፡፡*

- የምንኖረው ማንም በሰውነቱ ላይ የወደደውን እንዲያደርግ በተፈቀደበት በነጻ ዓለም ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን ይኽ ትክክል ነው? ኦርቶዶክሳውያን ሰውነታቸውን በተላያዩ ቀለማት እንዲበጡ እንዲነቀሱ ተፈቅዶላቸዋል?

- ታቱ ወይም ሰውነትን መበጣትና መነቃቀስ ከአሕዛብ የተወረሰ ነው፡፡ ታቱ Hepatitis B and C, Tetanus, HIV ለመሳሰሉ በደም ዑደት ለሚተላለፉ በሽታዎችም ያጋልጣል፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካን አገር Hepatitis B ከጠፋ በኋላ ታቱ በሕጋዊ መንገድ በ1997 ሲፈቀድ አገርሽቶ ነበር፡፡

# መግቢያ…

- እስከ ዛሬም ድረስ የአሜሪካ ቀይ መስቀል የተነቀሱ ወይም ታቱ የተደረጉ ሰዎች እስከ 12 ወራት ድረስ ደም ከመለገስ ይከለክላሉ፡፡

- ከሁሉም በላይ በመጨረሻ ስንነሳ ጌታችን ለቶማስ እንዳሳየው በሰውነታችን ያደረግነውን የታቱ አውሬ… እንደያዝንም እንነሳለን፡፡ አስቀድመን በንስሐ ካልፋቅነውም ያስጠይቀናል፡፡ *ዮሐ 20፡25-27፡፡*

- በአገራችንም የጥነቱ ንቅሳት ፋሽን ሆኖ ከ10 ሺ ብር በላይ ድረስ እየተከፈለበት ወጣቶች ይልቁኑ ወጣት ሴቶች የሚደረግባቸውን ቤቶች በወረፋ ማጨናነቅ ይዘዋል፡፡ በአካላቸውም ላይ የቢራቢሮ፤ የእባብ የዘንዶ… ያስነቅሳሉ፡፡

- ንቅሳቱን ወይም ታቱውን ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ (የሚለቅ ወይም የማይለቅ) በማለት በታዘዙት መሠረት ይሠራሉ፡፡ በተለይ ቋሚውን ለማድረግ የመጡ እንዲያስቡበት ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ የእጮኛቸውን ስም በአንገታቸው ሥር አስነቅሰው ተጣልተው ሳይጋቡ ቢለያዩ በቀላሉ አይጠፋም… ይቀመጥም ቢባል አዲሷ መጠየቅዋ አይቀርም፡፡ ይህም የአደጋውን ከፍተኛነት ያስታውሳል፡፡

- ይኽን ሥራ የሚሠራው በከተማችን የሚገኘው ሰው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ወደሱ ሲሄዱ ቤተሰቦቻቸውን እንዲያማክሩ እያደረገ መሆኑን አንዳንዶች ይገልጹለታል፡፡

# ታቱ - አካልን መነቀስና በተለያዩ ቀለማት መበጣት

- ሰውነትን መነቀስና መበሳት በብሉይ የባርነት ምልክት ነበር፡፡

- ታቱ ማለት፡ ምልክት ማድረግ፤ ቅርጽ መሳል፤ መቆረጥ የተላያዩ ቀለማት ባላቸው መሳሪያዎች ሰውነትን መበጣት ወይም መበሳት ነው፡፡

- እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ሕግ #ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፡፡ በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፡፡ አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና፡፡; ይላል፡፡ ዘጸአት 20፡3-6፤ ዮሐ 14፡23፡፡

- እግዚአብሔር ለሰው በሰጠው ሕግና ትእዛዝ መሠረት ሰውነትን መበጣት ወይም መነቀስ አልተፈቀደም፡፡

- ዘሌዋ 19፡1-2 እና 19፡28 #ሥጋችሁን አትንጩ፥ ገላችሁንም አትንቀሱት እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡; እንዲሁም ዘሌዋ 21፡5 #ራሳቸውን አይላጩ፥ ጢማቸውንም አይላጩ፥ ሥጋቸውንም አይንጩ፡፡; ይላሉ፡፡ ይኸም መነቀስንና ሰውነትን መበጣትን የተመለከተ ሆኖ ይተረጎማል፡፡ ማቴ 5፡17-20፤ ሮሜ 7፡12

# ታቱ - አካልን መነቀስና በተለያዩ ቀለማት መበጣት…

- እንዲህ ያሉትም #ታላላቆችና ታናናሾች በዚህች ምድር ይሞታሉ አይቀበሩም ሰዎችም አያለቅሱላቸውም ስለ እነርሱም ገላን አይነጩላቸውም ራስንም አይላጩላቸውም፡፡; ኤር 16፡6፡፡ ተብሎላቸዋል፡፡

- መበጣት ወይም መነቀስ ተነቅሰው በሥዕል ላስቀመጡት ነገር ተገዢ መሆንን ስለሚያመለክት መጻሕፍት ሲከለክሉ እናነባለን፡፡

- መበሳት፡ ማለት ሕመም እስኪሰማ ድረስ ተጭኖ በስለት ሰውነትን መብሳት ነው፡፡ ስለዚህም ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ #ባሪያውም፡፡ ጌታዬን ሚስቴን ልጆቼንም እወድዳለሁ፥ አርነት አልወጣም ብሎ ቢናገር፥ ጌታው ወደ ፈራጆች ይውሰደው፥ ወደ ደጁም ወደ መቃኑ አቅርቦ ጆሮውን በወስፌ ይብሳው ለዘላለምም ባሪያው ይሁን፡፡; ይላል፡፡ ዘጸአት 21፡5፡፡

- ጆሮን መበሳትም የዘላለም ባርነት ምልክት ነበር፡፡ የእስራኤላውያን የዘላለም ባርነት በራሳቸው ፈቃድ ወይም ጥያቄ የሚከሰት ነበር፡፡ እስራኤላውያን አንዳንድ ጊዜ ይገጥማቸው በነበረው የኢኮኖሚ ችግር የተነሳ ባሮች ቋሚ ዋስትናን ይሹ ነበር፡፡ #እርሱ ግን አንተንና ቤትህን ስለወደደ፥ ከአንተም ጋር መልካም ስለ ሆነለት፡ ልወጣ አልወድድም ቢል፥ አንተ ወስፌ ወስደህ በቤትህ በር ላይ ጆሮውን ትበሳዋለህ፥ለዘላለምም ባሪያ ይሆንልሃል፡፡ በሴት ባሪያህ ደግሞ እንዲሁ ታደርጋለህ፡፡; ዘዳግም 15፡16-176፡፡

# ታቱ - አካልን መነቀስና በተለያዩ ቀለማት መበጣት…

- ቅዱስ ጳውሎስ "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" ብሏል። <u>*1ኛ ቆሮ 6፡19*</u>

- የክርስቲያኖች ሰውነት በመንፈስ ቅዱስ ስለተቀደሰ የእግዚአብሔር ነው። ይህንንም ሰውነት ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር እንጂ ለሌላ እንዲሰጡት አልተፈቀደላቸውም። በምንም መንገድ - በማጤስ፤ በመስከር፤ በመነቀስ፤ በቁማር ሊያጠፉትም መብት የላቸውም። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆንና የከበረ ደሙም መፍሰስ የተገዙ የእግዚአብሔር ውድ ገንዘቦች ናቸው።

- ክርስቲያኖች ሰውነታቸውን የተቀደሰ አድርገው የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሲሆን ባይወጡም የሚጠየቁ መሆናቸው ተገልጦአል።

- "ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ <u>ቢያፈርስ</u> እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።" <u>*1ኛ ቆሮ 3፡17።*</u>

# ጥያቄ

*፲በእጃችን ወይም በክንዳችን ላይ የምንነቀሰው የመስቀል ንቅሳትስ እንዴት ይታያል?*

- እኛ በፈቃዳችን በደስታ ለእግዚአብሔር ራሳችንን ተገዢ እናደርጋለን፤ ሙሉ ለሙሉም በእርሱ የምንደገፍ የምንታመንበትም እናደርጋለን፡፡ ይኸም ከፈቃደኝነት የመነጨ ግዴታ የሌለበት ነው፡፡ ገዢያችን እግዚአብሔርን እንወደዋለን ያለርሱም ነጻነት የሌለን መሆኑን እናምናለን፡፡ #ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ…; *ሮሜ 1፡1፡፡*

*በእግዚአብሔርና በሰይጣን ምልክት መካከል ያለው ልዩነት፡-*

- የእግዚአብሔር ምልክት *በሕዝቅኤል 9፡4 እና በራእይ 7፡3* ላይ የተጻፈውን የተመረኮዘ ነው፡፡ *በራእይ 13፡16* ከተጻፈው የአውሬውም ማኅተም/ምልክትም ይለያል፡፡

- #እግዚአብሔርም፦ በከተማይቱ በኢየሩሳሌም መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኵሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው፡፡; *ሕዝ 9፡4*፤ #የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው፡፡; *ራእይ 7፡3፡፡*

# ጥያቄ…

- እነዚህ ሁለት ምልክቶች ሰዎችን በሁለት ይከፍላሉ፡፡
  1. የእግዚአብሔር የሆኑት አማንያን ከመጨረሻው የፍርድ ቀን መከራ የሚጠብቃቸው በግንባራቸው የተደረገ ምልክት አላቸው፡፡
  2. ለሰይጣን የሚገዙት ደግሞ የእግዚአብሔርን ማኅተም በመቃወም የአውሬውን ማኅተም በሰውነታቸው ላይ በማድረግ ራሳቸውን ለአውሬው አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡

*ማጠቃለያ*

- ጆሮን መበሳት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነቱ ይልቅ ባሕላዊ ገጽታው የሚያደላ ሲሆን በፋሽን የተነሳ ሌላውን የሰውነት ክፍል መበጣት ግን ያልተፈቀደ መሆኑን እንገንዘብ፡፡
- ፋሽኑም ሲያልፍ ቀድሞ በተነቀሱት ንቅሳታቸው እንደሚሸማቀቁ እንደ አንዳንዶቹ ሰውነታችሁ በየቦታው በመበሳሳቱ ወደፊት ምቾት የማይሰማችሁ ስለ መሆኑ እርግጠኛ ሁኑ፡፡
- እንግዲህ በዙሪያችሁ ለሚገኙት ሁሉ በበጎ ሕይወት ምሳሌ ሁኑ፡፡ #የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለምአትምሰሉ፡፡; *ሮሜ 12፡2፡፡*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።